የአማራ ኅብረተሰብ ቅርስ በሚኔሶታ | Amhara Heritage Society of Minnesota
1821 University Ave W, St. Paul, MN 55104 Suit S-340
Ph: 763-291-2501 email: amharaMN@gmail.com www.amharaMN.org

ሰኔ 25 2012 ዓ.ም

Ref. # PR0003

# የአቋም መግለጫ

የአማራ ህብረተሰብ ቅርስ በሚኔሶታ በአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን በመግለጽ የአዲስ አበባ ፖሊስ እና የፌደራል ፖሊስ ግልጽነት በተሞላበት እና ፈጣን በሆነ ሁኔታ የወንጀል ምርመራውን አከናውኖ ወንጀለኞቹን ለፍርድ እንዲያቀርብ መግለጫ ማውጣታችን ይታወሳል።

ነገር ግን ይህንን የተፈጠረውን አሳዛኝ ሁኔታ ለፖለቲካ እና ለዘር ተኮር ጥቃት መጠቀም የሚፈልጉ አካላት በተቀነባበረ መልኩ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተማዎች በሚኖሩ የአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ጥቃት የመፈጸም እና ንብረት የማውደም ድርጊት እየፈጸሙ መሆኑን ተረድተናል። የማጣራቱ ሂደት ገና ባልተጠናቀቀበት እና ገዳዮቹ እነማን እንደሆኑ ባልታወቀበት ሁኔታ አማራ ላይ ያተኮረ የጥቃት ዘመቻ እየተደረገ መሆኑ እጅግ ያሳዘነን እና ያስቆጣን መሆኑን እየገለጽን በአማራ ላይ ጥቃት እንዲሰነዘር የሚያነሳሱ እና ድርጊቱንም በተግባር የሚፈጽሙ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ከዚህ እኩይ አላማቸው እንዲታቀቡ እናሳስባለን።

መላው ኢትዮጵያዊም ይህንን አሳዛኝ ክስተት ለግል አጀንዳቸው ለመጠቀም በሚፈልጉ እና ብሔርን ከብሔር በማጋጨት አገርን ለማፍረስ በተነሱ ጥቂት የኢትዮጵያ ጠላቶች የተጎነጎነ ተንኮል እና የጥፋት ወጥመድ መሆኑን ተረድቶ በዚህ ጭንቅ ቀን ከአማራው ወገኑ ጎን በመቆም ከጥቃት ይከላከለው እና የአገሩንም አንድነት ይታደግ ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን።

ኢትዮጵያን እግዚያብሔር ይባርካት!
የአማራ ህብረተሰብ ቅርስ በሚኔሶታ